## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ሁለተኛው ትውልድ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

## የክትባት አገልግሎት ፓኬጅ

ሐምሌ 2007 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1
2. ዓላማ ........ 1
2.1. አጠቃላይዓላማ ........ 1
2.2. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 1
3. የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበር ........ 2
3.1. ዕቅድ ማዘጋጀት ........ 2
3.2. ግንዛቤና ባለቤትነት መፍጠር ........ 2
3.2.1. ግንዛቤማሳደግ ........ 2
3.2.2. ባላቤትነት ማሳደግ ........ 2
3.2.3. ለክትባት የታለሙ የህብረተሰብ ክፍሎች መከተባቸውን ማረጋገጥ ........ 3
3.2.4. ከሌሎች ዘርፎች ጋር በትብብር መስራት ........ 3
3.3. የአገልግሎት ሂደት ........ 4
3.3.1. የአገልግሎት ቅድመ-ዝግጅት ........ 4
3.3.3 የአገልግሎት አሰጣጥ ........ 4
3.4. የቅዝቃዜ ሰንሰለትን መጠበቅና መከታተል ........ 5
3.6. ለኮልድ ቦክስና ቫክሲን ኬሪየር የአይስ ፓክስ አጠቃቀምና የክትባት መድኃኒቶች አያያዝ 8
4. የአግልግሎት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ........ 9
4.1 የአገልግሎት ክትትል ........ 9
4.2 የአገልግሎት ግምገማ ........ 9
4.3 በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች ቅኝትና አሰሳ ማካሄድ ........ 9
5 አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ........ 10
5.1 ግብዓቶች ........ 10
6 በአጠቃላይ ከአገልግሎቱ የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 11
7 የአገልግሎቱ ዋና ዋና ጠቋሚዎች ........ 11

# 1. መግቢያ

በአገራችንበአሁኑ ወቅት በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው ተላላፊ በሽታዎች ቁጥር አስር ደርሷል፡፡ይህም ማለትአንድ ህጻን ክትባትን በትክክል ከተከተበ ከአስር አይነት ተላለፊ በሽታዎች የተጠበቀ ይሆናል ማለት ነው፡፡ እነዚህም በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች ቲቢ፣ኩፍኝ/አንከሊስ፣ዘጊአናዳ፣ትክትክ፣ የልጅነት ልምሻ፤በሮታ ቫይረስ የሚመጣ ተቅማጥ፣የሳምባምች፣ ተላላፊ የጉበት በሽታ፤ በሄሞፍለስ እንፉሉዌንዛታይፐ B የሚመጣ የማጅራት ገትር እና መንጋጋ ቆልፍ ሲሆኑ እነዚህ በሕፃናት ጤና ላይ ከፍተኛ የጤና ችግር የሚያስከትሉ ናቸው፡፡

የክትባት ኘሮግራሙ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተያዙትን የፖሊዮ በሽታ የማጥፋት፣ የመንጋጋ ቆልፍ፣ የኩፍኝ እና ሌሎች ከላይ የተጠቀሱ በሽታዎች ህመምና ሞት የመቀነስ እና የመቆጣጠር ሥራዎች ይዞ ይንቀሳቀሰል፡፡ እንዲሁም በኘሮግራሙ ያሉ እና ለወደፊቱ የሚጨመሩ አዳዲስ ክትባቶች ከፍተኛ ሽፋን የማድረስ እቅድ ይዟል፡፡

በሀገር ደረጃ እና በአንዳንድ ክልሎች ያለው ሽፋን የተሻለ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁንና ሁሉም ህፃናት ሙሉ በሙሉ የክትባት ተጠቃሚ አልሆኑም፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች የክትባት አገልግሎት ሽፋን ዝቀተኛ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የክትባት አግልግሎት ሽፋን የሚያሳዩ መረጃዎች የወጥነትና የጥራትም ችግሮች ይታያሉ፡፡

ስለሆነም በቀጣይ የክትባት አገልግሎት ተደራሽነት በማሳደግ ሁሉም ህጻናት የሁሉም የክትባት አገልግሎት እንዲሁም ክትባት ማግኘት የሚገባቸውን እናቶች በጥራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል ይቻል ዘንድ ሁለተኛው ትውልድ የክትባት አግልግሎት ፓኬጅ ተዘጋጅቷል፡፡

# 2. ዓላማ

## 2.1. አጠቃላይዓላማ

ሁሉንም ህፃናት እና ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ሴቶችን በክትባት ልንከለከላቸው ከምንችላቸው በሽታዎች መከላከል

## 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የህብረተሰቡን አስተሳሰብ ማሳደግ እንዲሁም እውቀት መጨመር፤
- የህብረሰቡ ተሳትፎ እና ባለቤትነትን በማሳደግ የክትባት ተጠቃሚነትን ማሻሻል፤
- ለህጻናት የክትባት አገልግሎትን በጥራት መስጠት በክትባት ልንከለከላቸው ከምንችላቸው በሽታዎች መከላከል፤
- ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ሴቶች የመንጋጋ ቆልፍ ክትባት አገልግሎት በመስጠት ራሳቸውንና የሚወልዷቸውን ህፃናት ከመንጋጋ ቆልፍ በሽታ መካለከል፤

## 3. የሚከናወኑ ተግባራትና አተገባበር

### 3.1. ዕቅድ ማዘጋጀት

- ከልማት ቡድን አባላት ጋር በመቀናጀት በየጊዜው በቀበሌው/በጤና ኬላው ስር ያሉትን ነፍሰጡር እናቶች እና ከአንድ አመት በታች የሆኑ ህፃናት መመዝገብ፤
- በቀበሌው/በጤና ኬላው ስር ከሚገኘው ህብረተሰብ ለክትባት አገልግሎት በቀላሉ ተደራሽ የማይሆኑ ህፃናትንና ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ሴቶችን መለየት
- ክትባቱን የሚሰጥበት ቦታ፤ ጊዜ፤ እንዲሁም መንገድማመቻቸት
- በቀበሌው በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች በቅርቡ ተከስተው እንደሆነ ለወደፊቱ ችግሩ እንይከሰት የማስተካካያ እርምጃን ማካተት፤
- የክትባት አገልግሎቱን ለማዳረስ የቀበሌውን የተለያዩ አደረጃጀቶች በመጠቀም ወሳኝ የሆኑ አካላትን መለየት እና መመዝገብ
- ዕቅዱን ለህብረተሰቡ፤ በተለይ፤ ለሴቶች ጤና ልማት ሰራዊት አባላትና ለቀበሌ ምክር ቤት አባላት፤ ለዘርፍ መ/ቤቶችና ሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ በማቅረብ መወያየት፤ በሚሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ተስተካክሎ እንዲፀድቅ ማድረግ፤
- የፀደቀውን ዕቅድ በሳምንት በወርና በሩብ አመት በመከፋፈል ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ/ማዳረስ፤

### 3.2. ግንዛቤና ባለቤትነት መፍጠር

#### 3.2.1. ግንዛቤማሳደግ

በቀበሌው በዋናነት  ልማት ሰራዊት እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ አደረጃጀች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን የህዝብ አደረጃጀቶች በመጠቀም ለህብረተሰቡ በቀላሉ የጤና መረጃ ለማድረስ ትልቅ አቅም ናቸው፡፡

- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዋ በቀበሌው የተደራጁ የሴቶች ልማት ሰራዊት አደረጃጀቶችን እንዲሁም ሌሎች አደረጃጀቶችን መለየት፤ መመዝገብና መጠቀም፤
- ያልተደረጁትን ማደረጃት፤ የተደራጁትን ማጠናከር፤ የተሻለ አፈጻፀም ያላቸውን ማበረታታት፤ ወደ ተግባር ያልገቡትን ወደ ተግባር ማስገባት፤ ድጋፍ ካስፈለገ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤ ሁሉንም ቤተሰብ የሚወክሉ የህብረተሰብ ክፍሎች መደራጀታቸውንና፤  አደረጃጀቶች እየሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ  ያስፈልጋል፡፡

#### 3.2.2. ባላቤትነት ማሳደግ

በክትባት ስለምንከላከላቸው በሽታዎች ግንዛቤ መኖር ወሳኝ ቢሆንም ነገር ግን ብቻውን በራሱ  መተግበርን ላያመለክት ይችላል፡፡ ስለሆነም ከእውቀት በተጨማሪ የህብረተሰቡን አመለካከት፣ ክህሎትና የመተግበር አቅም ማሳደግ ተገቢ ይሆናል፡፡ ለማሳወቅ አንዱ ዘዴ ፊት ለፊት መማማር ነው፡፡ የፊት ለፊት መማማር ላይ የጤና ኤክሰቴንሽን ባለሙያዋ ከፍተኛ የመሪነት ድርሻ አላት፡፡

- እያንዳንዱ በቀበሌው ነዋሪ የሆነ ሰው በክትባት ዙሪያ ያለውን የዕውቀት፤ የአመለካከት፤ የባህሪ ክፍተት መለየት፤
- በተለዩ ክፍተቶችን መሰረትስለክትባት ጠቀሜታ፤ ክትባት ስለሚከላከላቸውን በሽታዎች፤ ክትባት ከወሰዱ በኂላ አልፎ አልፎ ሊከሰቱ ስለሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ምን ማድረግ እንደሚገባ ወዘተ ማስረዳት፤
- በተለይ ለሴቶች የልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት መሪዎችን በቤተሰብ ጤና መመሪያ ወይም ሌላ የክትባት የትምህርት መርጃ መሣሪያ መሰረት በማድረግ ማብቃት
- በክትባት ዙሪያ ወላጆች/አሳዳጊዎችና ሌሎች ተንከባካቢዎች፤ የሴቶች ልማት ቡድንና የአንድ ለአምስት መሪዎች እንዲሁም የሌሎች አደረጃጀቶች መሪዎች ሚና ምን እንደሆነ ማስጨበጥ፤
- ማስከተብና መከተብ ለህፃናት እና ለእናቶች ጤና ጠቃሚ መሆኑን፤ ለማስከተብም ሆነ ለመከተብ ዝግጁ መሆናቸውንና መተግበር እንደሚችሉ ማረጋገጥ፤

### 3.2.3. ለክትባት የታለሙ የህብረተሰብ ክፍሎች መከተባቸውን ማረጋገጥ

- በቀበሌው ስር ባሉ መንደሮች ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸውህፃናት እና እናቶች መዝግቦ መያዝ፤ ይህንንም በዋናነት ልማት ሰራዊት አደረጃጀቶችን በመጠቀም በየወቅቱ ማግኘት ይቻላል፤
- በቀበሌው በክትባት አገልግሎት ታላሚ ተከታቢዎችን ትንበያ አኃዝ ማዘጋጀት፣ ጥቅልና አመታዊ ጭማሪ ያላቸውን ታላሚዎች፣ የክትባት አፈፃፀም መለካት ክፍተት የተገኘባቸውን ታላሚዎች እንደክትባት አይነቱ መለየት፣
- የትኛው ቤት/መንደር ነዋሪዎች የክትባት አገልግሎት ይጠቃማሉ? የትኞቹ አይጠቀሙም? ለምን አይጠቀሙም? የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት ካሉ የክትባት አገልግሎት አገኝተዋል ወይ? ካለገኙ ለምን አላገኙም? ጀምረዉ ያቋረጡትን ለምን አቋረጡ? የሚሉ ጥያቄዎች በመለየት ተገቢውን መፍትሔ መስጠት፤

### 3.2.4. ከሌሎች ዘርፎች ጋር በትብብር መስራት

- በቀበሌው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር የክትባትና የሌሎች ጤና አገልግሎት መልዕክቶችን ማስተላለፍ፤
- በቀበሌው ከሚገኙ የሐይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማህበራት ጋር ሁሉም ህፃናት ክትባት እንዲያገኙ ተቀናጅቶ መስራት
- አዲስ የተወለዱ ህፃናት እንዲመዘገቡ የልደት ሰርትፍኬት እንዲያገኙ የተመዘገቡትም የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ በቀበሌው ከተመደቡ የወሳኝ ኩነቶች ሰራተኞች ጋር ተቀናጅቶ መስራት
- በቀበሌው ካሉ የግብርና የተለያዩ ድርጅቶች ወይም ተቋማት/ ጋር በጋራ መስራት

## 3.3. የአገልግሎት ሂደት

የክትባት አገልግሎት ለመስጠት የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

### 3.3.1. የአገልግሎት ቅድመ-ዝግጅት

- የእለቱን የክትባት ሥራ በተመለከተ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ተወካዮች የሥራ ክፍፍል (በቀኑ ክትባት ያላቸውን ሕጻናትና ሴቶች በስም ለይቶ በየጎጡ መስጠት) ማድረግ፤የቀሩትን ካሉ እንዲመጡ ማስታወስ
- ተከታቢዎች የሚያርፉበትን ቦታ በተቻለ መጠን ምቾት በሚሰጥ መልኩ ማዘጋጀት፤
- ክትባቶች ቅዝቃዜ፣ ሙቀት እና ብርሃን በማይደረስበት ቦታ በአግባቡ ማስቀመጥ፤ ቫክሲን ኬሪየር፣ የቀዘቀዙ (በረዶ የሰሩ) አይስ ፖኮች፤ የክትባት መስጫ መርፌ፤ ሲሪንጅ (ሶሎ ሹት)፣ ሴፍቲ ቦክስ፤ የአምፒውሎች መቁረጫ፣ ፋይልና ጥጥ (በውሃ የረጠበ)ማዘጋጀት፤ ለስራ ዝግጁ መሆናቸው ማረጋገጥ እና በተገቢው ሁኔታ ማስቀመጥ፤
- ሁል ጊዜ ለክትባት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን እና ቅጾችን ማዘጋጀት፤
- አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ክትባት በጤና ኬላው እንዲኖር ማድረግ፤ ማመቻቸት፤
- ክትባቱ በአቅራቢያዉ ካለው የጤና ጣቢያ የሚመጣ ከሆነ ለቀኑ የሚያስፈልገውን መጠን ብቻ ማምጣት
- በየቀኑ የሚሰጠው አጭርና ግልጽ ትምህርት ማዘጋጀት
- የክትባት መድኃኒቶች ትክክለኛና ያልተበላሹ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ለምሳሌ ቪቪም (VVM) ማየት፤በአንቲጅን የሚገኘው አራትማዕዝኑውስጥየነበረውነጭምልክትበዙሪያውካለውግራጫክብመልክጋርከተመሳሰለ ወይም ይበልጥ ከጠቆረአለመጠቀም
- የክትባት አሰጣጥ ሥርዓት ባለው ሁኔታ እንዲከናወን አስቀድሞ ማዘጋጀት፣

### 3.3.3 የአገልግሎት አሰጣጥ

- ምዝገባ እና ታሊ ማድረግ እንዲሁም አዳዲስ ተከታቢዎችን መመዝገብ ለድጋሜ ክትባት የመጡትን መለየት
- መድኃኒቶች በፀሐይ እንዳይጎዱ እና በበረዶም እንዳይጎዱ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ፣
- አስፈላጊው ዝግጅትና ሥርዓት ተጠብቆ ተከታቢዎች ተራ በተራ ክትባቱን እንዲወስዱ ማድረግ
- በቀጣይ መቼ ማስከተብ/መከተብ እንዳለባቸው ማሳወቅ እና የቀጠሮ ወረቀት መስጠት፣
- ክትባቱ የተሰጠበት መርፌና ሲሪንጅ በአግባቡ በሴፍቲ ቦክስ ውስጥ መጨመሩን ማረጋገጥ፣
- ያልተከተቡ ካሉ መቼ የት እንደሚወሰዱ መወሰን እና አገልግሎቱ መሰጠት፣
- ምናልባት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወደ ክትባት አግልግሎት መስጫ ቦታ መምጣት ያልቻሉ መሆናቸው ከታመነ ወደ ቤት ሄዶ መስጠት፣
- የክትባት አግልገሎት ከተሰጠ በኋላ ቆሻሻዎች መወገዳቸውን ማረጋገጥ፣


- ❖ የተረፉ ክትባቶች(ፖሊዮ እና ቴታነስ) የቅዝቃዜ ወሰን እንደተጠበቀ ወደ ፍሪጅ መመለስ
- ❖ ወደ ፍርጅ የማይመለሱ እና ከተከፈቱ ስድስት ሰአት ከሆናቸው የሚጣሉትን ክትባቶች ካሉ ወደ ፍርጅ እንዳይመለሱ ለብቻው በማስቀመጥ እና የሚወገድበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ሪፖርት ማድረግ
- ❖ ክትባት ጀምረው ያቋረጡ ካሉ ለይቶ  አገልግሎት የሚወስዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ❖ የእለቱ የክትባት ሥራ ከተጠናቀቀ በኂላ ክፍሉን፣እቃዎችንና አካባቢውን በአግባቡ ማጽዳት
- ❖ የክትባት ጎናዊ ጉዳቶችን እና በቤት የሚደረጉ እንክብካቤዎች ለአስከታቢዎች ማሳወቅ
- ❖ የተለዩ ችግር (ለምሳሌ፡ AEFI) ያለባቸው ሕፃናት ካሉ አስፈላጊውን እርዳታ መስጠት፣
- ❖ የክትባት አገልግሎትን ሳይቆራረጥ መስጠት፤
- ❖ ክትባታቸውን ላጠናቀቁ ሰርተፊኬት መስጠት፣

## 3.4. የቅዝቃዜ ሰንሰለትን መጠበቅና መከታተል

- ○ የፍሪጅ አቀማመጥ ከግድግዳው ከ30–50 ሣ.ሜትር ርቀት፣ ከወለሉ ደግሞ ከ5–10 ሣ.ሜትር ከፍታ ላይ መቀመጥ አለበት፣
- ○ ለክትባት የምንጠቀምባቸው አይስ ፓኮች በበረዶ ክፍል ማስቀመጥ
- ○ የፖሊዮ፤ የሚዝል እና የቢሲጂ ክትባቶች ከላይኛው መደርደሪያ ማስቀመጥ፣
- ○ የፔንታ፤ሮታ፤ቲቲፒሲቪ ክትባት መድኃኒቶች ከመካከለኛው መደርደሪያ እና መበጥበጫዎች ከታችኛው መደርደሪያ ማስቀመጥ፣
- ○ መደርደሪያዎች በክትባት ከተሞሉ ግን መበጥበጫውን ከፍሪጅ ውጭ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ክትባት ከመስጠታችን በፊት ውጭ የተቀመጠውን መበጥበጫ ከታችኛው የፍሪጅ ክፍል በማስገባት እንዲቀዘቅዝ ማድረግ፤ሆኖም ግን መበጥበጫዎች ከፍሪጅ ውጭ እንደተቀመጡ አንስቶ ለክትባት መበጥበጫ መጠቀም ክትባቱን ስለሚጎዳው 24 ሰዓት ቀደም ብሎ ፍርጅ ውስጥ በማስገባት ለመበጥበጫነት መጠቀም፤
- ○ ከታችኛው መደርደሪያ  ውኃ የተሞላ አይስ ፓክስ  ማስቀመጥ የፍሪጁን ቅዝቃዜ ለመጠበቅ ስለሚረዳ ውኃ የተሞላ አይስ ፓክስ ማስቀመጥ፣
- ○ በፍሪጅ ውስጥ ያላግባብ የገገረ በረዶ ማቅለጥ
- ○ ሁሉም የክትባት መድኃኒቶች ከ 2 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እስከ 8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ (+2 0C እስከ +8 0C) መካከል መጠበቅ
- ○ ፍሪጁ ሁልጊዜ በትክክለኛው የሙቀት ወሰን መሆኑን ማረጋገጥና በቀን ሁለት ጊዜ በተለይ ጥዋትና ማታ የሙቀት መጠኑን መመዝገብ ወይም ዲጂታል የሙቀት መቆጣጠሪያን ማስቀመጥ፣
- ○ ድንገተኛ ብልሽት የሚያገጥም ከሆነ የክትባት መድኃኒቶችን በቫክሲን ኬርየር መያዣ የቅዝቃዜ መጠናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአቅራቢያው ወዳለው ጤና ተቋም ማስተላለፍና የጥገና ባለሙያ መጠየቅ፣

- የክትባት አንቲጅኖችን ሊያበላሹ ከሚችሉ እንደ ሙቀት፣ የፀሃይ ብርሃን ፣ ቅዝቃዜ እና ከሚካሉች መከላከል
- የክትባት አንቲጅኖች ወደ ክትባት ጣቢያ ሲወሰዱ በትክክለኛ የክትባት ቁሶችኮልድ ቦክሶች ወይም ቫክሲን ኬሪየሮች የቅዝቃዜ ሰንሰለታቸው ጠብቆ ማጓጓዝ
- ክትባት በሚሰጥበት ጊዜ መድኃኒቶቹ በፎም ፓዶች ማስቀመጥ


**ስዕል 1የአንቲጅን ሪፍሪጅሪተር ስእላዊ መግለጫ**




**ስዕል 1፡ የክትባት መድሃቶች ማስቀመጫ ኮልድ ቦክስ**


**የቅዝቃዜ ሰንሰለት ቁሶች እና ቁልፍ መልእክቶቻቸው**

ሀ. ኮልድ ቦክስ የክትባት መድኃኒቶችን ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝና ፍሪጅ በሌለበት ወይም ፍሪጁ ሲበላሽ እስከ 72 ስዓት ድረስ ክትባተቶችን ሳይበላሹ ማቆየት የሚስችላል። የውስጡን ቅዝቃዜ መጠን ለመቆጣጠር የሚረዳ ቴርሞ ሜትር/ፍሪጅ ታግ በውስጡ ማስመቀመጥና ሙቀቱም ጠዋትና ማታ መመዝገብ አለበት።



ስዕል 2፡ የክትባት መድሃኒቶች ማስቀመጫ ኮልድ ቦክስ

ለ. ቫክሲን ኬሪየር በአግባቡ በደንብ በአይስ ፓክስ በበቂ ሁኔታ በአራቱም ማእዝኖች የውስጥ ክፍሉ ከተሞላ የክትባት መድኃኒቶችን ለ24 ሰዓት ማቆየት ያስችላል። ወደ በረዶነት የተለወጠ አይስ ፓክስ ለክትባት ሁሉ ጥሩ ነው ተብሎ ይታሰብ ነበር፤ሆኖም ግን ክትባቶች የሚፈልጉት የቅዝቃዜ መጠን እንደ ክትባቱ አይነት ስለሚለያይ እንደ ፔንታና ቲቲ ክትባቶች በረዶነት በተለወጠ አይስ ፓክስ ቢጓጓዙ ስለሚበላሹ በቀዝቃዛ አይስ ፓክስ መጓጓዝ አለባቸው።ስለሆነም የክትባት መድኃኒቶች ከጤና ኬላ ውጪ ሲጓጓዙ የውስጡን የቅዝቃዜ መጠን ለመቆጣጠር የሚረዳ ቴርሞ ሜትር ወይም ፍሪጅታግ በውስጡ ማስቀመጥ።



ስዕላዊ መግለጫ 3፡ የክትባት መስቀመጫ ቫክሲን ኬሪየር

## 3.5. የፍሪጅ ቅዝቃዜን ለማስተካከል የአጠቃቀም ዘዴዎች

### ሀ. ቅዝቃዜው ከ 2 ዲግሪ ሴንት ግሬድ በታች ከሆነ

- በረዶ ክፍሉ በተገቢው መዘጋቱን ማረጋገጥና መገጣጠሚያዎቹ ችግር ካለባቸው ፈትሾ መፍትሔ መስጠት፣
- የሙቀት መቆጣጠሪያውን/ቴርሞ ስታት/ መጨመር፣
- በቅዝቃዜ በቀላሉ የሚበላሹ የክትባት መድኃኒቶችን/ፔንታቫለንትእና ቲቲን/ በመነቅነቅ አለመርጋቱን ማረጋገጥ፣
- ፍሪጁ በረዶ ሰርቶ ከሆነ ማቅለጥ፣
- ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሄ እርምጃዎች ወስደው ማስተካከል ካልቻለ መድኃኒቶችን ወደ ኮልድቦክስ ማዛወር፡፡

### ለ. ሙቀቱ ከ 8 ዲግሪ ሴንት ግሬድ በላይ ከሆነ

- ፍሪጁ እየሰራ መሆኑን፣ነጭ ጋዝ አለማለቁን ወይም የኤለክትሪክ ኃይል አለመቋረጡን ማረጋገጥ፣
- የሙቀት መቆጣጠሪያውን/ቴርሞስታት/ መቀነስ፣
- ፍሪጅ ታግ ፍሪጅ ውስጥ ማስቀመጥ መከታታልና አላርም ሲያሳይ እርምጃ መውሰድ፣
- በሮች በደንብ መዘጋታቸውን ማረጋገጥና መገጣጠሚያዎቹ ችግር ካለባቸው ፈትሾ መፍትሔ መስጠት፣
- ከላይ የተጠቀሱት የመፍትሄ እርምጃዎች ተወሰደው ማስተካከል ካልቻለ መድኃኒቶችን ወደ ኮልድቦክስ ማዛወር፡፡

### ሐ. በፍሪጅ ውስጥ ያላግባብ የገገረ በረዶ ማቅለጥ

- በሙቀት እና በቅዝቃዜ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ መድኃኒቶችን በማውጣት አይስፓክ ወዳለው ኮልድ ቦክስ ማዛወር ፣
- የፍሪጁን መብራት ማጥፋት፣
- በሩን በመክፈት በረዶው እንዲቀልጥ ማድረግ፣
- የፍሪጁን ውስጥና መገጣጠሚያዎችን በንፁህ ጨርቅ ማጽዳት፣
- ፍሪጁን እንደገና መለኮስ፣
- ቅዝቃዜው በሚፈለግበት መጠን ሲሆን መድኃኒቶችን መመለስ፡፡

## 3.6. ለኮልድ ቦክስና ቫክሲን ኬሪየር የአይስ ፓክስ አጠቃቀምና የክትባት መድኃኒቶች አያያዝ

- በረዶ የሰሩትን አይስ ፓክስ ከፍሪጅ ውስጥ ማውጣትና በአግባቡ ማስቀመጥ
- በመጠኑ የቀለጡትን አይስ ፓክስ በአራቱም አቅጣጫና ከታች ማስቀመጥ
- የክትባት መድኃኒቱንና መበጥበጫውን መሀል መደርደር
- የቅዝቃዜ መለኪያ ቴርሞሜትሩን መድኃኒቱ ላይ ማስቀመጥ
- የቀለጠ  አይስ ፓክስን በመድኃኒቱ ላይ ማድረግ
- መሸፈኛ ስፖንጅ ከላይ በማድረግ ክዳኑን በትክክል መግጠም

## 4. የአግልግሎት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

የክትባት አገልግሎት ክትትልና ግምገማ በየጊዜው ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም የክትባት አገልግሎት አፈፃፀምን በየጊዜው መከታተልና መገምገም ያስፈልጋል፡፡

### 4.1 የአገልግሎት ክትትል

- ከቀበሌ አስተዳደር ተወካዮች፣ ከክላስተር ጤና ጣቢያ ባለሙያዎች፣ ከሴቶች የጤና ልማት ቡድን አባላት እና ከሌሎች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ተወካዮች በጋራ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- ተጨባጭና እውነታውን የሚያመላክቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ መተንተን፣ በአግባቡ ማደራጃትና መጠቀም፣
- ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ህፃናትና ሴቶች ወቅቱን ጠብቆ በመርሐ ግብራቸው መሰረት የክትባት አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን መከታተል፣
- የቀበሌውን የክትባት ሽፋን መከታተያ ቻርት በየወቅቱ በአግባቡ መስራትና ወቅታዊ ማድረግ፣
- ሪፍረጅሬተር ካለ በትክክለኛው የሙቀት መጠን ወሰን (ከ 2 እስከ 8 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ) ውስጥ መሆኑን እንዲሁም ለክትባት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች መኖራቸውን መከታተል፣
- የክትባት መድኃኒቶች ለወር በቂ መሆናቸውን፣ ጥቅም ላይ የዋለና የባከነ መድኃኒት መጠንን ከመስፈርቱ ጋር በመነፃፀር መከታተል፣
- ለክትትሉ ዋና ዋና አመለካቾችን ወይም ጠቋሚዎችን በጤና መረጃ ስርዓት መሰረት ከሚሰበሰቡት ውስጥ መመረጥና መከታተል፣
- የክትባት አገልግሎት ተጠቃሚዎችን አስተያየትና መጠየቅና የሚሰጡትን ግብረ መልስ ለስራ ማሻሻያ ለግብዓትነት መጠቀም፣
- የተጠናከረ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለግብዓት በሆነ መልኩ መጠቀም፡፡

### 4.2 የአገልግሎት ግምገማ

- ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ተጠቃሚዎች ስለክትባቱ ያላቸውን እውቀት፤አመለካከትና ተግባር መዳሰስ፣
- የክትባት አገልግሎትን አፈፃፀም ከዕቅድ አንፃር መፈተሽና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣
- በየወሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማለትም የህብረተሰብ ተወካዮች፣ የዘርፍ መ/ቤት ተወካዮች የቀበሌ አመራርና የጤና ጣቢያ ባለሙያዎች በተገኙበት የጤና አገልግሎት አሰጣጥን መገምገም ከህበረተሰቡ ግበረ መልስ መውሰድ፣
- በግምገማው ወቅት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን መለየት፣ ለወደፊቱ ዘላቂና ቀጣይ ለማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ የድርጊት መርሐ ግብር መንደፍና ከባለድረሻ አካላት ጋር ስራ ተከፋፍሎ መስራት፡፡

## 4.3 በክትባት ልንከላከላቸው የምንችላቸው በሽታዎች ቅኝትና አሰሳ ማካሄድ

የበሽታ ቅኝት መረጃን መሰብሰብ፤ መተንተን፤ መተረጎምን፣ መጠቀም እንዲሁም ለሚመለከተው አካል ለውሳኔና ለእርምጃ ማስተላለፍን ያጠቃልላል፡፡

በክትባት የምንከላከላቸው በሽታዎች አልፎ አልፎ በወረርሽኝ መልክ ሊከሰቱ የሚችሉባቸው አጋጣሚዎች አሉ። በተለይም እንደ ኩፍኝ፤ ፖሊዮ፤ ትክትክ፤ቲታነስና ማጅራት ገትር በሽታዎች በስፋት ሊከሰቱ ይችላሉ።

ስለዚህም የበሽታዎች ቅኝትና ዳሰሳ ሲካሔድ፡-

- በመመሪያ መሰረት ቅኝት ማድረግ፣
- በየመንደሩና በየጎጡ ያሉ የልማት ሠራዊት አባላት ማንኛዉንም የበሽታ ክስተት ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የበሽታዎች ጭምጭምታ ካለ በጭምጭምታ መመዝገብና ማጣራት፣
- በሽታዉ ከተከሰተ የማህበረሰብ የበሽታ መገለጫ/ትርጉም ያላቸው ዕውቀት በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ፤ መተንተን፣ግብረ-መልስ መስጠትና መቀበል እንዲሁም በአስቸኳይ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፣

# 5 አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

የክትባት አገልግሎት ለመስጠት በጤና ኬላ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች የሚከተሉት ናቸው።

## 5.1 ግብዓቶች

### ሀ. የመዛግብትና የሪፖርት ቅፃቅፆች

የቤተሰብ የጤና መረጃ መሰብሰቢያ፣የቲክለር ቦክስ፣ታሊ ሺት፣የሪፖርት መላኪያና መቀበያ ቅፆች፣የክትባት ካርድ እና የክትባት መከታታያ ቻርት፤

### ለ. የክትባት ትምህርትና መግባቢያ መርጃ መሳሪያዎች

የቤተሰብ ጤና መመሪያ፣የክትባት አገልግሎት አፈጻጸም መመርያ፤ የክትባት የጎንዮሽ ችግር መከታተያ መመርያ/Adverse Event Following immunization Guideline/፤ Immunization in practice፤ የክትባት አገልግሎት ፓኬጅ፤ የተቀናጀ የክትባት ማሰልጠኛ ሞዱል/ EPI IRT module/፤ የኩፍኝ፣ የማጅራት ገትርና የፖሊዮ የማጠናከሪያ ክትባት የአፈጻጸም መመሪያዎች፣ የክትባት ፖስተሮች ፤ የክትባት ፍሊፕ ቻርቶች፤ በራሪ ወረቀቶች ወዘተ…

### ሐ. የቅዝቃዜ ሰንሰለት ለማስጠበቅ የሚረዱ ግብአቶች

- ፍሪጅ
- ኮልድ ቦክስ
- ቫክሲን ኬሪየር
- አይስ ፓክስ
- ቴርሞ ሜትር
- ፍሪጅ ታግ

### መ. የክትባትመድኃኒቶች እና ሌሎች ቁሳቁሶች

- በአፍ የሚሰጥ ፖሊዮ የክትባት መድኃኒት ከነድሮፐሩ
- ሚዝልስ ከነመበጥበጫው፣ መበጥበጫና መውጊያ ኤዲ ስሪንጅ

- ቢሲጂ ከነመበጥበጫውና መውጊያ ስሪንጅ
- ፔንታና ኤዲ ስሪንጅ፣
- ፒሲቪ ሲሪንጅ፣
- ኤች.ፒ.ቪ./ የማህፀን በር ካንሰር መከላከያ ክትባትና ስሪንጅ
- ሮታ ከነድሮፐሩ
- ቲቲና ኤዲ ስሪንጅ
- የፖሊዮ የክትባት መድኃኒት
- ሴፍቲ ቦክስ
- ጥጥ
- የክትባት እቃዎች መያዣ ቦርሳ
- አልኮሆል፣ በረኪና
- ጠረጴዛ እና ወንበር
- ሚዛን

**ረ. የእጅ መታጠቢያ**

- ውሃ
- ሣሙና
- ፎጣ

# 6 በአጠቃላይ ከአገልግሎቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በክትባት በምንከላከላቸው በሽታዎች እና በክትባት ጠቀሜታ ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ፤ተሳትፎና ባለቤትነት ያድጋል፣
- ሁሉም ህጻናትና ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ሴቶች የክትባት አገልግሎት በጥራትና በፍትሀዊነት ተጠቃሚ ይሆናሉ፤
- ህጻናትን ከቲቢ፣ ተላላፊ የጉበት በሽታ፣ ከመንጋጋ ቆልፍ፣ ከዘጊ አናዳ፣ ከትክትክ፣ ኩፍኝ፤ ከልጅነት ልምሻ፤በኢንፍሊዌንዛ ታይፕ ቢ የሚመጣ የማጅራት ገትር፣ የሳንባ ምች፤ በሮታ ቫይረስ ከሚመጣ ተቅማት በሽታ፣ አካለ ጉዳት መከላከል ብሎም ሞት ይቀነሳል፣
- የልጅነት ልምሻ በሽታ ይወገዳል፤
- የኩፍኝ፣የማጅራት ገትርና የእናቶችና የጨቅላ ህፃናት መንጋጋ ቆልፍ በሽታዎች በወረርሽኝ መልክ መከሰት ይቀንሳል፡፡

# 7 የአገልግሎቱ ዋና ዋና ጠቋሚዎች

- በቀበሌው ከሚገኙ አዲስ የተወለዱ ህፃናት ቢሲጂ እና በአፍ የሚሰጥ ፖሊዮ 0 ክትባት የወሰዱ፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የፔንታ 1፣ በአፍ የሚሰጥ ፖሊዮ 1፣ ፒሲቪ 1፣ ሮታ 1 ክትባት የወሰዱ
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የፔንታ 2፣ በአፍ የሚሰጥ ፖሊዮ 2፣ ፒሲቪ 2፣ ሮታ 2 ክትባት የወሰዱ፣

- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የፔንታ 3፣ፖሊዮ 3፣ በመርፌ የሚሰጥ ፖሊዮ፣ ፒሲቪ 3 ክትባት የወሰዱ፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት የኩፍኝ ክትባት የወሰዱ፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ከአንድ ዓመት በታች ህፃናት ሀሉንም የክትባት ዓይነቶች ወስደው የጨረሱ፣
- በቀበሌው ከሚገኙ ዕድሜያቸው ከ15-49 የሆኑትን ሴቶች የቲቲ (ቲቲ2፣ቲቲ 3፣ቲቲ4፣ ቲቲ5) ክትባት የወሰዱ፣
- ከመንጋጋ ቆልፍ በሽታ ተጠብቀዉ የተወለዱ ህጻናት፣
- በቀበሌው ክትባት ጀምረው ያቋረጡ (ህጻናትና ክትባት ማግኘት የሚጠበቅባቸው ሴቶች)፣
- በጤና ኬላው የክትባት ብክነት መጠን፣
- በቀበሌው ምንም ክትባት ያልወሰዱ ህጻናት፣
- የሚላኩ ሪፖርቶች ወቅታዊነትና ሙሉነት፣